በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# <u>እመቤታችንን ማክበር</u>

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ማክበር ነፍሳችን የምትታመንበት የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን አንዱ ቁልፍ አስተምሕሮ ነው፡፡
- ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ለተወሰኑ ሳምንታት የምንማረው ስለ እመቤበተችን ይሆናል፡፡
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ክርስትና ከተመሠረተበት ዘመን አንስቶ የተቸገሩትን በመርዳትዋ፣ አምላካችን ሰውን ለማዳን ባደረገው ጉዞ ታላቅ ድርሻ ስለነበራትና በእግዚአብሔርም ዘንድ በተወደደው ንጽሕናዋ፣ ሕይወትዋ፣…በክርስቲያኖች ዘንድ ልዩ ክብር የተሰጣት ከመሆኑ በተጨማሪ ክርስቲያኖች ከፍ ያለ አድናቆትና ፍቅር አለን፡፡ በአማላጅነትዋም እናምናለን፡፡
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ማክበር ቅዱስ ገብርኤል ‹‹ደስ ይበልሽ፥ <u>***ጸጋ የሞላብሽ***</u> ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ …፡፡» <u>***ሉቃስ 1፡28፡፡***</u> በማለት አምላክን እንደምትወልድ ካበሰረበት ጊዜ ጀምሮ ተገልጧል፡፡
- ቅዱስ ገብርኤል ይህን ሰላምታ ከሰጠ ከጥቂት ቀናት በኋላ ቅድስት ኤልሳቤጥ ‹‹አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፥ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፡፡» ሉቃ 1፡42 በማለት እመቤታችንን አመስግናለች፡፡
- ቅዱስ ሉቃስ በወንጌሉ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የጌታ እናት መሆንዋን መንፈስቅዱስ የገለጠላት መሆኑን ገልጦ ጽፎልናል፡፡ <u>***ሉቃስ 1፡28-42፡፡***</u>
- ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በእመቤታችን ሕይወት የተደረጉትን የምናስብባቸው ዕለታትና በዓላት በመወሰን የሰጠቻትን ክብር ገልጣለች፡፡
- በጸሎታችንም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ ብለን እንጠራታለን፡፡ ከጽንሰት ጀምሮ በማኅፀንዋ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ቆይቶ የተወለደው እውነተኛው አምላካችን ነውና፡፡ ‹‹… ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ፡፡ … በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለላም ይነግሣል፥ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም፡፡» <u>***ሉቃ 1፡31-33፡፡***</u> እንደተባለ ፡፡

# <u>እመቤታችንን ማክበር</u>

- ብዙዎች የሚሆኑ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት፣ መምህራን፣ ሰባክያን… ስለ እመቤታችን ክብር የምስጋና መዝሙራትን፣ ግጥሞችን፣ የጸሎት መጻህፍትን፣ ትምህርቶችን፣ … ጽፈው አቅርበዋል፣ ዘምረዋል፣ … የዛሬዎቹም ይህንኑ በሚመስል ሕይወት እንገኛለን፡፡
- በነዚህ ትምህርትና ምስጋና የተነሳ እንዴት እንደኖረች፣ በአምላክዋ ፊት የተወደደው ውበትዋ ምን እንደነበር፣ አምላክ እንዲዋሐዳት ያበቃት የተመረጠችበት ምን እንደሆነ፣ በአማላጅነትዋ እንድንታመን የሚያደርገን ምን እንደሆነ ስለምንማር ሁላችን ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም በቅዳሴው፣ በመዝሙሩ፣ … ‹‹ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል» <u>*ሉቃ 1፡48*</u>እንዳለ ክብር እንሰጣታለን፣ እናመሰግናታለን፡፡
- ብዙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የእግዚአብሔር ልጅ ለሰው ልጅ መዳን መሳሪያ ካደረጋት ድንግል እንደሚወለድ አስቀድመው ተንብየዋል፡፡
- የመጀመሪያውን ስለ ድንግሊቱ (ልዩ ስለሆነች ሴቲቱ) የተነገረውን ቃልኪዳን የሰሙት አዳምና ሔዋን ናቸው፡፡
- እግዚአብሔር ሰይጣንን ‹‹ በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና <u>*በዘርዋም መካከል*</u> ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ፡፡» <u>*ዘፍጥ 3፡15*</u> ብሎታል፡፡
- በብሉይ የዘር ሐረግ የሚቆጠረው በወንድ በኩል ነበር፡፡ አዳኙ መሲሕ ግን የሴቲቱ ዘር ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ ይህም በሥጋ የሚወልደው አባት እንደሌለው እግዚአብሔር ወልድ በዳግም ልደት ያለ አባት ከእናት - ከእመቤታችን እንደሚወለድ የሚያሳይ የመጀመሪያው ምልክት ወይም ትንቢት ነው፡፡
- ከብዙ ዘመናት በኋላ ነቢዩ ኢሳይያስ « ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ፥ <u>*ድንግል ትፀንሳለች*</u>፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች፡፡» <u>*ኢሳ 7፡14፡፡*</u> ለመጀመሪያው ትንቢት የሚሆን ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡
- አይሁድ ለማመን የሚቸገሩበት ቢሆንም ‹‹ድንግል›› የሚለውን ‹‹ሴት›› በሚለው ሳይተካ የተነገረው ትንቢት ሲፈጸም አሳይቷቸዋል፡፡ የተወለደውም መሲህ ራሱ እግዚአብሔር ነበር፡፡ <u>*ሉቃ 1፡35*</u> በዚህም የተነሳ እመቤታችንን ወላዲተ አምላክ እንላታለን፡፡

# የእመቤታችን ሕይወት

- ቀድመው ከተጻፉት የክርስቲያኖች መጻሕፍት እንደምናነበው ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ እመቤታችንን ስለሚያውቃት በወንጌሉ መንፈስቅዱስ ያስረዳውን እናትነትዋን እንዳንዘነጋ አድርጎ ደጋግሞ ጽፎልናል፡፡
- ቅዱስ ሉቃስ ሐኪምና ሰዓሊ ነበር፡፡ ለእመቤታችንም ካለው ፍቅር የተነሳ ሥዕልዋን ሥሎ ነበር፡፡ እርሱም ከሳላት በኋላ ሌሎች አስመስለው ስለዋል፡፡ … በቤተ ክርስቲያናችን … ኦ ርኅርኅተ ኅሊና እንተ ሰዓላ በእዱ፤ ሉቃስ ጠቢብ እምወንጌላውያን አሐዱ ብለን መልክአ ሥዕል በተባለው ጸሎት የምናነሳው ከዚህ የተነሳ ነው፡፡

## ልደቷ

- አዳኙ መድኃኒት እግዚአብሔር ሰው የሚሆንበት ዘመን ሲቃረብ በናዝሬት ገሊላ ከሚኖሩ ሁለት ቅዱሳን እመቤታችን ተወልዳለች፡፡ ‹‹ የናዝሬቱ ኢየሱስን…» ተብሎ የተጻፈልን በዚሁ ምክንያትም ነው፡፡ ***ዮሐ 18፡7፣ ሉቃ 2፡51፡፡***
- አባቷ ቅዱስ ኢያቄም እናቷም ቅድስት ሐና የሚባሉ በደግነታቸውና በርኅራኄያቸው የሚታወቁ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ቅዱሳን ነበሩ፡፡ ቅዱስ ኢያቄም ከንጉሡ ከዳዊት ወገን የነበረ ሲሆን ልጅ ሳይኖራቸው እስከ እርጅና ዘመናቸው ደርሰው ነበር፡፡ ‹‹ *መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው…*» ***መዝ 86፡1፡፡***
- ልጅ ለመውለድ የነበራቸው ዕድል እጅግ ጥቂት የነበረ ቢሆንም እግዚአብሔርን ከመጠየቅ ግን አልተከለከሉም ነበር፡፡
- የምትሰጠንንም ልጅ ለቤተ መቅደስ አገልግሎት እንሰጣለን ብለው ወደ እግዚአብሔር እንደ ነቢዩ ሳሙኤል እናት ተሳሉ፡፡ ***ቀዳ ሳሙ 1፡11፡፡***
- በዚያ ዘመን ልጅ አለመውለድ ስለ ኃጢአት በእግዚአብሔር መቀጣትን ያመለክት ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ትዕግሥታቸውንና እምነታቸውን አይቶ ታላቅ ደስታን አደረገላቸው፤ ቅድስት ሐና ሴት ልጅ ወለደች፤ ስምዋንም ማርያም ብለው ጠሩ፡፡

# የእመቤታችን ሕይወት

*__ወደ ቤተ መቅደስ መግባትዋ__*

- እመቤታችን ሦስት ዓመት ሲሆናት እግዚአብሔርን የሚፈሩ ቅዱስ ኢያቄምና ቅድስት ሐና ስዕለታቸውን ለመፈጸም ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ይዘዋት ሄዱ፡፡ ‹‹ሰነፎች ደስ አያሰኙትምና ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ ትፈጽመው ዘንድ አትዘግይ የተሳልኸውን ፈጽመው፡፡» *__መክ 5፡4፡፡__*
- በቤተ መቅደስም እንደርስዋ ላሉ ደናግል ለትምህርት እንዲሆን በተዘጋጀው ሥፍራ እንድትማርና ካህኑ ዘካርያስ አደራውን ተቀብሎ ትተዋት ተመለሱ፡፡ ‹‹በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ፤ ሚስቱም ከአሮን ልጆች ነበረች፥ ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበረ፡፡» ሉቃ 1፡5፡፡
- እመቤታችንም የእግዚአብሔርን ሕግ እየተማረች፣ በእጅዋም ፈትልን እየፈተለች፣ ከመጻሕፍት የተገኘውን ጸሎት እየጸለየች አሥራ ሁለት ዓመት በቤተ መቅደስ ኖረች፡፡
- እመቤታችን በቤተ መቅደሱ በንጽሕና በቅድስና ኖረች እንጂ፤ በዚያ ዘመን እንደነበሩ አንገታቸውን እንደሚያገዝፉ ዕብራውያን ሴቶች እድፍ የምታውቅ አልነበረችም፡፡
- እግዚአብሔርንም ለማገልገል ድንግል ሆና ልትኖር ተስላ ራስዋን ለእግዚአብሔር ብቻ ሰጠች፡፡ ፈጠሪዋንም እያገለገለች ብቻ ልትኖር መረጠች፡፡ ‹‹… ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ *__ታጨች__* ወደ *__አንዲት ድንግል__* ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፥ *__የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ__*፡፡ *__ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል__*? አለችው፡፡» *__ሉቃ 127-34__* ሲተረጎም የሚነግረን እውነት ድንግል ሆና ልትኖር ራስዋን ለእግዚአብሔር በስዕለት መስጠትዋን ነው፡፡

# የእመቤታችን ሕይወት

***ለዮሴፍ መታጨትዋ***

- ቅዱስ ኢያቄምና ቅድስት ሐና እመቤታችን ለቤተ መቅደስ እንደሰጡ ብዙ ሳይቆዩ አርፈው ነበርና እመቤታችን ያለ እናትና አባት በቤተ መቅደስ አሥራ አምስት ዓመት እስኪሆናት ድረስ ኖረች፡፡
- እንደ ሕጋቸውም ከዚህ በላይ መቆየት ስለማትችል ሊቀ ካህኑ ስዕለትዋን በማሰብ በታማኝነት ሊጠብቃት ፈቃዱ ለሆነው፣ ከዳዊት ወገን ለተገኘው፣ ዕጣውም ለደረሰው ለአረጋዊው ለዮሴፍ አጫት፡፡
- « የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ፡፡ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች፡፡ እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ፡፡ እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ፡፡ ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ፡፡ በነቢይ ከጌታ ዘንድ፡፡ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም፡፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው፡፡ ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ፤ እጮኛውንም ወሰደ፤ የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ስሙንም ኢየሱስ አለው፡፡» ***ማቴ 1፡18-25፡፡***
- ዘመድዋ አረጋዊው ዮሴፍም አናጢ የነበረ ሲሆን ቀድሞ የወለዳቸው ልጆቹ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም ይባሉ ነበር፡፡ እነርሱም እኛም ከምንጋራው ባሕላቸው የተነሳ ወንድሞቹ ተብለው በአይሁድ ተጠቅሰዋል፡፡ አይሁድ ስም አይጥቀሱ እንጂ እህቶቹም ብለው የጠሩአቸው ነበሩ….
- « ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን? እኅቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን? እንኪያስ ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው? ***ተሰናከሉበትም***፡፡ ኢየሱስ ግን፦ ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ቤቱ በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው፡፡ በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም፡፡ » ***ማቴ 13፡55-56፡፡*** እንደተባለው እመቤታችን ንጹሕ ሆና የጠበቃት የአረጋዊው ዮሴፍን ቤት ባዕትዋ አድርጋ በድንግልና ኖራለች፡፡

# <u>የእመቤታችን ሕይወት</u>

<u>*ብሥራተ ቅዱስ ገብርኤል*</u>

- ቅዱስ ገብርኤል ለዘካርያስ ከተገለጠለት ከስድስት ወር በኋላ የሚያስደስት ዜናን ይዞ በገሊላ ናዝሬት ወደምትገኘው ወደ እመቤታችን ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ። መልአኩም እመቤታችንን ዓለምን የሚያድነውን መድኃኒትን እንደምትወልድ አበሠራት። <u>*ሉቃ 1፡8-25፣ ሉቃ 1፡26-48።*</u>
- መልአኩም ለእመቤታችን ተገልጾ ‹‹ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት፡፡»
- እመቤታችንም የቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ከማንና ከየት እንደሆነ መረመረች።
- ቅዱስ ገብርኤልም በመቀጠል ‹‹ ማርያም ሆይ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለላም ይነግሣል፥ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም፡፡» አላት፡፡
- እመቤታችንም በቅዱስ ገብርኤል ንግግር በመገረም ‹‹ ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው፡፡»
- መልአኩም ሁሉ የሚደረገው ወይም የሚሆነው ሁሉን በሚችለው በእግዚአብሔር እንደሆነ ‹‹ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ፥ እርስዋ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፥ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወር ነው፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና። » በማለት መለሰላት፡፡

# የእመቤታችን ሕይወት

## *ብሥራተ ቅዱስ ገብርኤል*

- እመቤታችንም ‹‹ እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች፡፡» *ሉቃስ 1፡26-28፡፡*
- ከዚህ ቃልም በኋላ ቃል - እግዚአብሔር ወልድ በማኅጸንዋ ተጸነሰ፡፡
- በዚህም በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ታላቅ ተአምር ታይቷል፤ ተደርጓል፡፡ የማይወሰነው አምላክ የሚወሰነውን ሥጋ ለበሰ፡፡ መላእክት የማይደርሱበት ምጡቅ ብርሃን የሆነ እርሱ ወደ እመቤታችን ማኅጸን ወረደ፡፡
- የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ይህን የመጽሐፍ ክፍል ሲተረጉሙ ሔዋን የእባብን ቃል ሰምታ መታለልዋን በማሰብ እመቤታችን የቅዱስ ገብርኤልን ሰላምታን ቃል ስትሰማ ያሳየችውን ጥበብ እንድናደንቅ በሚያደርግ መልኩ ተርጉመውታል፡፡
- እመቤታችን እናቱ መሆንዋን እግዚአብሔር ቢወስንም፤ ለሰው ሁሉና ለሰውም የሰጠውን ነጻ ፈቃድ ሳይጋፋ የእርስዋ ፈቃደኝነት እንዲታይ አድርጓል፡፡ ይህም ፈቃደኝነትዋ በሰው ልጅ መዳን ያላትን ታላቅ ሱታፌ የሚያሳይ ነው፡፡

## *እመቤታችን ቅድስት ኤልሳቤጥን መጠየቅዋ*

- የካህኑ የዘካርያስ ሚስት ዘመድዋ ኤልሳቤጥ ልትወልድ መድረስዋን እመቤታችን ስትሰማ ፈጥና ልትጠይቃት ወጣች፡፡
- ወደ ኤልሳቤጥም ቤት ገብታ ኤልሳቤጥን እንዴት ነሽ? አለቻት፡፡ ኤልሳቤጥም የእመቤታችን ማርያምን ድምጽ ስትሰማ መንፈስ ቅዱስ ሞልቶባት እመቤታችን የጌታ እናት መሆንዋን ተረዳች፡፡ *ሉቃስ 1፡41፡፡*

# የእመቤታችን ሕይወት

***እመቤታችን ቅድስት ኤልሳቤጥን መጠየቅዋ***

- **ኤልሳቤጥም ድምጽዋን ከፍ አድርጋ በማልቀስ ‹‹አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፥ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?» አለቻት፡፡**
- **እመቤታችንም « ነፍሴ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች ፤ የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና ፤ ስሙም ቅዱስ ነው። ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል።»  *<u>ሉቃ 1፡46-50</u>* በማለት ለኤልሳቤጥ በሰጠቻት መልስ እግዚአብሔርን አከብራለች፡፡**
- **እመቤታችን በቅድስት ኤልሳቤጥ ዘንድ ሦስት ወር ከቆየች በኋላ ወደ ናዝሬት ተመለሰች፡፡**
- **አረጋዊው ዮሴፍ እመቤታችን መጽነስዋን ሲያውቅ ደንግጦ አንድ የማያውቀው ነገር እየተደረገ እንደሆነ በመገመት ከሆነው ሊርቅ አሰበ፡፡**
- **የአይሁድ ሕግ ባለመታመን የተገኙ ሚስቶችን በድንጋይ ተወግረው እንዲገደሉ ያዛል፡፡ *<u>ዮሐ 8፡1-11፡፡</u>***
- **እግዚአብሔርም የተደረገውን « እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ። እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ።» ማቴ 1፡1-21 ብሎ በመልአኩ አስረድቶታል፡፡**

# የእመቤታችን ሕይወት

***እመቤታችን ቅድስት ኤልሳቤጥን መጠየቅዋ***

- በማስከተልም «ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።» ብሎ ስም እንዲያወጣለት አዘዘው። ***ማቴ 1፡21፣ ኢሳ 7፡14።***
- በቅዱስ መጽሐፋችን ከልጅዋ ከጌታችን ሕይወት ጋር ስለ እመቤታችን ብዙ ተገልጦልናል።
- በቅዱስ መጽሐፋችን በቤተ ልሔም ከመወለዱ ጋር፣ በግዝረቱ፣ የጥበብ ሰዎች እጅ መንሻ ከማምጣታቸው ጋር፣ በ40ኛው ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ይዘው ካመጡት መሥዋዕት፣ ወደ ግብጽ በተደረገው ስደት፣ በናዝሬት ስለመኖራቸው፣ በአሥራ ሁለት ዓመቱ ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም በመሄዱ፣ በመስቀል ተሰቅሎ ሳለ፣… እመቤታችን አብራ ተገልጣለች ወይም ተብራርታለች። ***ማቴ 1፣ ማቴ 2፣ ሉቃ 1፣ ሉቃ 2፣ ማር 1፡9፣ ዮሐ 19፡25-27፣ …።***
- እነዚህም የቅዱስ መጽሐፋችን ቃላት ስለ እመቤታችን ትሕትና፣ እምነት፣ ትዕግሥት፣ ብርታት፣ ለእግዚአብሔር ስላላት ታማኝነትና ፍቅር፣ ለልጅዋም ስለከፈለችው መሥዋዕትነት ለአንባብያንና አማንያን ግልጥ ማረጋገጫ በመስጠት እውቀትን ያስጨብጣሉ። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንደተናገረው በእግዚአብሔር ዘንድ ያገኘችው ባለሟልነትዋ ይኸንኑ የሚገልጥ ነው። ***ሉቃ 1፡30።***
- በቃና ዘገሊላ የተደረገው የመጀመሪያው ተአምር በልጅዋ ላይ ልታሳድር የምትችለውን የእናትናት ተጽእኖ እና ርኅራኄዋን የሚያመለክት ነው። ***ዮሐ 2፡1-11።***
- ይህም ሕይወትዋ እመቤታችንን ለክርስቲያኖች ሁሉ ይልቁንም ለተገፉትና ለተጨቆኑት የላቀች አማላጅ ያደርጋታል።

# የእመቤታችን ሕይወት

***ቅድስት ኤልሳቤጥን መጠየቅዋ***

- ለሠርጉ የሚሆነው ወይን ያለቀባቸው መሆኑን በመገንዘብ የልጅዋን ትኩረት ወደ ጉዳዩ ስባለች፡፡ ልጅዋም ጥያቄዋን እንደማይንቅ ታውቅ ነበር፡፡
- አገልጋዮቹንም የሚላችሁን አድርጉ ብላ አዘዛቸው፡፡ ይህም የእመቤታችንና የጌታችን ጥያቄና መልስ ውጤቱ መልካም እንደሆነ የሚጠቁም ነው፡፡
- አዎ በርግጥም ይህ አማላጅነትዋ ብዙም በማይታወቁ በነዚህ ምስኪናን ሕይወት ውስጥ ትልቅ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት እንዲፈጠር አድርጎታል፡፡
- ይህም የጌታችን የመጀመሪያው ተአምር እንደሆነ ተመዝግቦልናል፡፡ ከዚህም በኋላ « ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ፡፡» *<u>ዮሐ 2፡11፡፡</u>*
- እርሱ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ለማዳን የመጣበትን ለመፈጸም ሲል ጥቅም አላደረገውም እንጂ ወንጌላት ስለእመቤታችን የሆነውን ሁሉ በልብዋ የምትጠብቅ፣ ለልጅዋ ልዩ ትኩረት የምትሰጥ፣ በሄደበት ሁሉ ተከትላው የምትሄድ፣ በሚያስፈልገው ሁሉ ያገለገለችው፣ እስከ ሠላሳ ዘመኑም ድረስ በእናትነት የሚደረገውን ሁሉ ያደረገች፣ ወዘተ ጽፈውልናል፡፡
- ለማስረዳት እንኳ በሚያስቸግረው ጌታችን በቀራንዮ በፈጸመው የማዳን ሥራ ሳትለይ ተገኝታ ለወዳጁ ለወንጌላዊው ለቅዱስ ዮሐንስ እናቱን አደራ ሰጥቷታል፡፡
- እመቤታችን በሚሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ከመስማማት በቀር የቁጣ ቃል ፈጽሞ ከአንደበትዋ አልወጣም ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ታላቅነትዋ የተገለጠ ቢሆንም ዛሬም ኦርቶዶክሳውያን የሆኑት ክርስቲያኖች ይህንኑ አክብረው ይገኛሉ፡፡

# <u>የእመቤታችን ሕይወት</u>

## *<u>ቅድስት ኤልሳቤጥን መጠየቅዋ</u>*

- በበዓለ ጰንጠቆስጤ መንፈስቅዱስ ወርዶ ደቀመዛሙርቱ ሁሉ በአዲስ ቋንቋ  ሲናገሩ እመቤታችን አብራ ነበረች፡፡
- ከጌታችን ስቅለት በኂላ እመቤታችን በዚህ ምድር የኖረችው አሥራ አምስት ዓመታት ነው፡፡
- ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ ሳለ ለቅዱስ ዮሐንስ እመቤታችንን እናት አድርጎ ሲሰጠው ልጅ ሆኖ እስከ ዕረፍትዋ ድረስ ሊንከባከባት ወደ ቤቱ ወሰዳት፡፡
- ከጌታችን ዕርገት በኂላ ሐዋርያት መንፈስቅዱስን ተቀብለው በየአህጉረ ስብከታቸው ተሰማርተው የክርስትና እምነት ሲስፋፋ ብዙዎች ክርስቲያኖች በሐዋርያት ዜና የሰሚትን እመቤታችንን ለማየትና ለማናገርም ከተለያዩ አገራት ወደ እርስዋ ይመጡ ነበር፡፡
- ዛሬ መቃብርዋ የሚገኝባትን ጌቴሴማኒን ለመሳለም ብዙዎች ወደ ኢየሩሳሌም እንደምንኼድ ሁሉ ከእረፍትዋ በፊት የነበሩ ክርስቲያኖች በአካል ከእመቤታችን ተገናኝተው በረከትን ለመሰብሰብ ወዳለችበት ይጎርፉ ነበር፡፡ ተገናኝተዋትም ድምጽዋን ሰምተዋል፣ ናፍቆታቸውን ተወጥተዋል፡፡
- ጌታችን ቅዱስ ዮሐንስን ልጅ አድርጎ ከሰጠበት ጊዜ አንስቶ የክርስቶስ ልጆች ወይም ተከታዮች ለሆን ሁሉ እመቤታችን እናታችን ናት፤ ልዩ ክብርም እንሰጣለን፡፡ «ጭፍሮችም እንዲህ አደረጉ፡፡ ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ፥ የእናቱም እኅት፥ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም፥ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር፡፡ ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን፡፡ አንቺ ሴት፥ እነሆ ልጅሽ አላት፡፡ ከዚህ በኂላ ደቀ መዝሙሩን፡፡ *<u>እናትህ እነኂት</u>* አለው፡፡ ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ *<u>ወደ ቤቱ ወሰዳት</u>*፡፡» *<u>ዮሐ 19፡25-27</u>* እንዳለ፡፡
- የእመቤታችን አማላጅነት ዘወትር አይለየን!!!
- አምላካችን እውነተኛው ፍቅር በልባችን እንዲታተም ፍቅርዋን በልባችን ያሳድርብን፡፡

# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም


## መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

E-mail: kesisolomon4@gmail.com


**ቦታ፡ ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**
**በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት** ከ12፡30 – 1፡30

**ሐምሌ** ፳፲ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም.

# ይቆየን…

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org